የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 15 እና 16

1. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል በወይን ሐረግ ምሳሌው ላይ የማያፈራ ቅርንጫፍ ምን እንደሚገጥመው ተናገረ?
ሀ)ይወገዳል
ለ)ይጠራል
ሐ)እንዲያፈራ ብዙ ጊዜ ይተዋል
መ)ሁሉም

2. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል በወይን ሐረግ ምሳሌው ላይ በእርሱ የማይኖር ደረቅ ቅርንጫፍ ምን ይደረጋል ብሎ ተናገረ?
ሀ)ወደ ውጭ ይጣላል
ለ)ይጠራል
ሐ)ተሰብስቦ ይቃጠላል
መ)ሀ እና ሐ

3. የመጨረሻ የፍቅር መግለጫ ተብሎ የተጠቀሰው ምንድን ነው?
ሀ)ራሱን የሚወድ ሰው
ለ)ስለወዳጆቹ ሲል ነፍሱን አሳልፎ ሚሰጥ
ሐ)ባርያውን እንደጌታው የሚያይ
መ)ሁሉም

4. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስሙ ያመኑ ሰዎችን በዓለም ዘንድ ምን እንደሚደርስባቸው ተናገረ?
ሀ)ዓለም ይወዳቸዋል
ለ)ዓለም ያከብራቸዋል
ሐ)ዓለም ይጠሏቸዋል
መ)ሀ እና ለ

5. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 15 "ከአብ የሚወጣ " በማለቱ ስለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ምን አስተማረን?
ሀ)ከአብ ብቻ እንደሚሰርፅ(እንደሚወጣ)
ለ)ምስክርነት እንደማይሰጥ
ሐ)እንደማያስተምር
መ)ሁሉም

6. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለም ስለሚደርስባቸው ግፍ አስቀድሞ ለሐዋርያት ለምን ነገራቸው?
ሀ)እንዲደሰቱ ስላልፈለገ
ለ)ጦር እንዲያዘጋጁ
ሐ)ከእርሱ እንዲሸሹ
መ)ፈተና ሲመጣ እንዳይሰናከሉ

7. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 16 ላይ የእርሱ ወደ አብ መሄድ ለሐዋርያት ምን እንደሆነ ነገራቸው?
ሀ)የሚያሳዝን ነገር እንደሆነ
ለ)ጥሩ እንደሆነ ጰራቅሊጦስን ስለሚልክላቸው
ሐ) መጥፎ መሆኑን እርሱ በመሄዱም ሊያዝኑ እንደሚገባ
መ)መልስ አልተሰጠም

8. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 16 ላይ "ጥቂት ጊዜ ታዩኛላችሁ" ብሎ የተናገረውን ሲያስረዳ በምን መስሎ አስረዳ?
ሀ)በወይን ሐረግ
ለ)በእርግብ እና በጎጆ
ሐ)በምጥ እና ልጅ መውለድ
መ)ሁሉም

9. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት በተውት ጊዜ
ሀ)ብቻውን ነበር
ለ)አብ ከርሱ ጋር ነበር
ሐ)ማንም አልነበረውም
መ)መልስ አልተሰጠም

10. ከሚከተሉት ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት በዓለም ሳሉ ይደርስባቸዋል ካለው ውስጥ ይመደባል?
ሀ)ያሳድዷቹሀል
ለ)ይገድሏችኋል
ሐ)ከምኩራብ ያስወጧችኋል
መ)ሁሉም

11. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ላይ ጌታ ሐዋርያትን ምን ብሎ ጠራቸው?
ሀ) ባሮች ለ)ሠራተኞች ሐ)ወዳጆች መ) መላእክት

12. ጌታ "በፍቅሬ ኑሩ " ሲል ምን ማለቱ ነው?
ሀ)እኔ ከወደድኳችሁ ይበቃልና እናንተ ልትወዱኝ አይገባም
ለ)እኔ ከወደድኳችሁ ይበቃልና እናንተ ባትዋደዱም ችግር የለውም
ሐ)እኔ እንደወደድኳችሁ እናንተም እርስ በእርሳችሁ ተዋደዱ
መ)ሀ እና ሐ

13. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ላይ የወይን ግንድ የሚንከባከበው ገበሬ የማን ምሳሌ ነው?
ሀ) ወልድ ለ)አብ ሐ)መንፈስ ቅዱስ መ)መልሱ የለም

14. የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ቁጥር 25 ላይ "በከንቱ ጠሉኝ" የሚለው ቃል ስለ አይሁድ ጌታን ያለ ምክንያት መጥላት የማን ትንቢት መፈጸሙን ያሳየናል?
ሀ)የኢሳይያስ ለ)የኤርምያስ ሐ)የንጉሥ ዳዊት መ)የሰሎሞን

15. ጌታ በ ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ላይ ሐዋርያትን "... ከዓለም ስለ አይደላችሁ ... " ያላቸው ለምንድነው?
ሀ)መላእክት ስለሆኑ
ለ)ከኃጢአተኛው ሕዝብ ስለተለዩ
ሐ)ሲወለዱ ጀምሮ በፍጹም እምነት ጌታን ስለተጠባበቁ
መ)ለ እና ሐ

16. በምዕራፍ 16 ላይ እንደተገለጠው ጌታ መንፈስ ቅዱስ ዓለምን ይወቅሳል የተባለው ስለምንድን ነው?
ሀ)ዓለም በኢየሱስ ክርስቶስ ባለማመኑ
ለ)ዓለም ጽድቅን ባለመቀበሉ
ሐ)ዓለም ለዲያብሎስ በመገዛቱ
መ)ሁሉም መልስ ናቸው

17. ጌታችን በምዕራፍ 16 ላይ “አብ እና እኔን ስላላወቁ ነው” ሲል ምን ማለቱ ነው?
ሀ)ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ስለማያውቁ ለማለት ነው
ለ)ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ፈጣሪ መሆኑን ስለማያውቁ ነው
ሐ)እግዚአብሔር የሚባል አምላክ ስለማያውቁ ነው
መ)ሀ እና ለ

18. ጌታችን በሚያዝበት ጊዜ ደቀመዛሙርቱ እንደሚበተኑ “እረኛውን ምታ መንጎቹም ይበተናሉ” ብሎ የተነበየው ነቢይ ማነው?
ሀ)ነቢዩ ኢሳይያስ ለ)ነቢዩ ዘካርያስ ሐ)ነቢዩ ሆሴዕ መ)ነቢዩ ኤርሚያስ

19."ጥቂት ጊዜ አለ አታዩኝምም " የተባለው ስለ የትኛው ጊዜ ነው?
ሀ)ከምሴተ ሐሙስ እስከ ትንሳኤ (አሑድ ጠዋት) ያለውን ጊዜ ነው
ለ)ከተወለደ እስከ ጥምቀቱ ድረስ ያለውን ጊዜ ነው
ሐ)ከትንሳኤ ጀምሮ በገሊላ ለሐዋርያት እስኪታያቸው ያለውን ጊዜ ነው
መ)ከትንሳኤ ጀምሮ በኤማሁስ እስኪገለጽ ድረስ ያለውን ጊዜ ነው

20. "ደግሞ ጥቂት ጊዜ አለ ታዩኛላችሁም" የተባለው ስለ የትኛው ጊዜ ነው?
ሀ) ስለ ስቅለት
ክለ)ስለ ደብረ ታቦር
ሐ)ከትንሳኤው እስከ ዕርገቱ ስላለው ጊዜ
መ)ለ እና ሐ